
በፕሬዘደንት
ዲየትር ኤፍ ኡክደርፍ
የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ



# ወንድምሆይ፣ ለእዚህ ህይወቴን አውላለሁ

ሁለት ወጣት ወንድሞች በጣም ንጹህ የሆነ የሀይቅ ውሀን ለመመልከት በሚቻልበት በትንሽ ኮረብታ ላይ ቆመው ነበር። ይህ ሰዎች ወደ ውሀው ዘለው የሚገቡበት ቦታ ነበር፣ እናም ወንድሞቹ ሌሎች አንዳንዴ ሲያደርጉት እንዳዩት ለመዝለል ብዙ ጊዜ ይነጋገሩበት ነበር።

ምንም እንኳን ለመዝለል ቢፈልጉም፣ ማንኛውም ለመዝለል የመጀመሪያ ለመሆን አልፈለጉም ነበር። የኮረብታው ከፍታ ታላቅ አልነበረም፣ ነገር ግን ለሁለቱ ወንዶች፣ ለማየት ወደፊት ሲመለከቱ ከፍታው እየጨመረ የሚሄድ ይመስላቸዋል፣ እናም ብርቱነታቸው በፍጥነት ይጠፋል።

በመጨረሻም፣ አንድ ወንድም እግሩን በኮረብታ ጫፍ አይ አደረገና በውሳኔ ወደፊት ሄደ። በእዚያም ጊዜ፣ ወንድሙ እንዲህ አለ፣ "ምናልባት እስከሚቀጥለው በጋ እንጠብቅ።"

የመጀመሪያው ወንድሙ የወደፊት መነቃነቁ ግን ወደፊት እየገፋው ነበር። "ወንድሜ፣ ለእዚህ ወስኛለሁ" ብሎ መለሰለት።

ወደ ውሀው ዘለለ እናም በድል እየጮኸ ወዲያው ከውሀው ወጣ። ሁለተኛው ወንድም ወዲያው ተከተለው። ከእዚያም በኋላ፣ ሁለቱም "ወንድሜ፣ ለእዚህ ወስኛለሁ" በማለት ስላለው የመጀመሪያው ልጅ የመጨረሻ ቃል ሳቁ።

የልብ ውሳኔም በትንሽ መንገድ ወደ ውሀው ውስጥ በመዝለል እንደ መግባት አይነት ነው። ውሳኔ አድርጋችኋል ወይም አላደረጋችሁም። ወደፊት ትሄዳላችሁ ወይም ባላችሁበት ቆማችሁኋል። የግማሽ መንገድ የለም። ሁላችንም ህይወታችንን በሙሉ የሚቀይሩ የውሳኔ ጊዜዎች ይኖሩናል። እንደ ቤተክርስቲያኗ አባላ፣ እራሳችንን "በመዝለል እገባለሁ ወይስ በጫፍ ላይ እቆማለሁ? ወደፊት እሄዳለሁ ወይስ በእግር ጣቴ የውሀውን ሙቀት እገምታለሁ?" ብለን መጠየቅ አለብን።

አንዳንድ ኃጢያቶች የሚሰሩት ስህተት የሆነውን በማድረጋችን ነው፤ ሌሎች ኃጢያቶች የሚሰሩት ምንም ባለማድረጋችን ነው። ለወንጌል በሙሉ ልብ ውሳኔ ተሳታፊ አለመሆን ወደ ንዴት፣ ተከፊነት፣ እና ወደ ጥፋተኛነት ይመራል። እኛ የቃል ኪዳን ህዝቦች ስለሆንን ይህ እኛን የሚመለከት መሆን አይገባውም። ስንጠመቅ እና ወደ ጌታ ቤት ስንገባ ከጌታጋር ቃል ኪዳን እንገባለን። ወንዶች እንደ ክህነት ባለስልጣን ሲሾሙ፣ ቃል ኪዳን ይገባሉ። ከጌታ ጋር የገባነውን ቃል ኪዳን ከማክበር በላይ ምንም አስፈላጊ የሆነ ነገር ሊኖር አይችልም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ራሄል እና ልያ ለያዕቆብ የሰጡትን መልስ እናስታውስ። ይህም ቀላልና ግልጽ እናም የልብ ውሳኔአቸውን የሚያሳይ ነበር፥ "እግዚአብሔር ያለህን ሁሉ አድርግ" Genesis 31:16።

በሙሉ ልባቸው ውሳኔ ያላደረጉት የሙሉ ምስክር፣ ደስታ፣ እና ሰላም በረከቶችን አይቀበሉም። የሰማይ መስኮቶችም በሙሉ አይከፈቱላቸውም ይሆናል። "አሁን 50 ፐርሰንት የልብ ውሳኔ አደርጋለሁ፣ ነገር ግን በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፣ በሙሉ ልቤ ውሳኔ አደርጋለሁ" ብሎ ማሰቡ ሞኝነት አይመስልምን?

ከጌታ ጋር ለገባናቸው ቃል ኪዳን ለማክበር ሙሉ ውሳኔ ማድረግ የመቀየራችን ፍሬ ነው። ለአዳኝና ለቤተክርስቲያኑ ያለን የሙሉ ልብ ውሳኔ ጸባያችንን ያሳድጋል እናም ከክርስቶስ

ጋር ስንገናኝ አቅፎን "መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ" እስከሚለን ድረስ መንፈሳችንን ያጠናክራል (Matthew 25:21)።

ለማድረግ በማሰብ እና በመስራት መካከል ልዩነት አለ። የልብ ውሳኔ ለማድረግ ብቻ የሚያስቡት በየጊዜው ምክን ያቶችን ያገኛሉ። በእውነትም የልብ ውሳኔ የሚያደርጉትም፣ ለእራሳቸው "አዎን፣ ይህ ለማቆየት ጥሩ ምክንያት ነው፣ ነገር ግን ቃል ኪዳን ገብቼአለሁ፣ እናም አደርጋለሁ ብዬ ቃል እንደገባሁት አደርጋለሁ" በማለት ፈተናቸውን ፊት ለፊት ይቋቋማሉ። ቅዱሳት መጻህፍትን ያጠናሉ እናም የሰማይ አባታቸውን አመራር ቅን በመሆን ይፈልጋሉ። የቤተክርስቲ ያን ጥሪዎችን ይቀበላሉም ያጎላሉም። በስብሰባዎቻቸውም ይሳተፋሉ። የቤት ለቤት እናም የሴቶች የቤት ለቤት ማስተማ ራቸውንም ያከናውናሉ።

በጀርመን አገር ምሳሌ እንዲህ ይላል፣ "ቃል ኪዳን እንደ ሙሉ ጨረቃ ነው። ወዲያው ካልተጠበቁ፣ ቀን በቀን ይቀ ንሳሉ።" እንደ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት፣ በደቀመዛሙርት መንገድ ለመጓዝ ውሳኔ አድርገናል። የአዳኛችን ምሳሌን ለመከተልም ውሳኔ አድርገናል። የጌታ ቤተክርስቲያን አባላት በሙሉ በነፍሳቸው ጥልቀት በመቀየርና የእግዚአብሔር መንግስትን ለመገንባት ውሳኔ በማድረግ ባላቸው ችሎታ ቢኖሩ እንዴት አለም ትባረክ እና ትቀየር እንደሆነ ገምቱ።

በአንዳንድ መንገዶች፣ እያንዳንዳችን ውህውን በሚመለ ከት የውሳኔ ቦታ ላይ እንቆማለን። እምነት እንዲኖረን፣ ወደ ፊት እንድንጓዝ፣ ፍርሀታችንን እና ጥርጣሬአችንን በብርቱነት እንድንቋቋም፣ እና ለእራሳችሁ "በልቤ ወስኛለሁ" እንድትሉ እጸልያለሁ።

### ከዚህ መልእክት ማስተማር

"ተማሪዎችን የወንጌል መሰረታዊ መመሪያዎች እንዲገባቸው የሚረዱበት አንዱ መንገድ ስዕል እንዲስሉ ማድረግ ነው። ስዕል መሳል ስለወንጌል ታሪኮችና መሰረታዊ መመሪያዎች የሚገባቸ ውን እና ስሜታቸውን ለመመርመርና ለመግለጽ ይፈቅድላቸዋል (*Teaching, No Greater Call* [1999]፣ 166)። አንቀጹን ለማንበብ፣ ለወንጌሉ ለመኖር ስለመወሰን መሰረታዊ መመሪያዎች ለመወያየት፣ እና ከእዚያም የሚፈልጉትን የልብ ውሳኔን የሚያሳይ የወንጌል መሳተፍ ስዕልን እንዲስሉ መጠየቅን አስ ቡበት። ትትንሽ ልጆች ምን መሳል እንደሚችሉ ሀሳብ መስጠት ያስፈልጋቸው ይሆናል።

## ወጣቶች

# ሁሉም መስጠት ይችላሉ

**በአሊሳ ሀንሰን**

የትምህርት ክፍሎችን፣ ማሰልጠኛዎችን፣ የበጋ እርፍት ሽር ሽርን፣ እና ሌሎችን አይነት በበጋ ለማድረግ የፈለኳቸውን ነገሮች ለማድረግ እንዴት ለመክፈል እንደምችል እጨነቅ ነበር። የማለቅስም ይመስለኝ ነበር። ከእዚያም በጌታ እምነት እንዲ ኖረኝ የተማርኳቸውን ነገሮች አስታወስኩኝ። ጉዳዩን በጌታ እጅ ለመተው እና የእርሱ ፈቃድ ከሆነ፣ እርሱ መንገዱን እንደሚሰጠኝ ለማመን ወሰንኩኝ።

ከእዚያም በኋላ ብዙ ጊዜ ሳያልፍ፣ እናቴ በእዚያ አመት ከስራ ያገኘሁትን ገና ያልተዘረዘረ የባንክ ቼክ አገኘች፣ እናም በሚቀጥ ለውም ቀን በፉክክር ሁለተኛ በመሆኔ ትንሽ የገንዘብ ሽልማት በደብዳቤ መጣልኝ። ይህም እግዚአብሔር ህያው እንደሆነ፣ እርሱ እኔን እንደሚወደኝና እንደሚያስብልኝ እናም እንደሚረዳኝ ታላቅ ምስክር ሆነልኝ።

ለሰማይ አባቴ እና ለአዳኝ በምስጋና እና በፍቅር ተሞላሁ። የምፈነዳም አይነት ስሜት ተሰማኝ። ምን አይነት ምስጋና እንዳለኝ ለማሳየት፣ እግዚአብሔርን ከሚቻለኝ ሁሉ በላይ ለማሞገስ፣ እና ይህን ስሜት ለመካፈል ፈለኩኝ። ሌሎች ዘፈን በመጻፍ፣ ግጥም በመጻፍ፣ ወይም ስዕል በመሳል ይህን አድርገዋል፣ ነገ ግን ማን ኛቸውን እነዚያን ነገሮች ለማድረግ ብቁ እንዳልህንኩ ተሰማኝ። ለምስጋና ብቁ የሆነ ላደርገው የምችለው አንድ ነገር ቢኖር ህይወ ቴን አሳልፌ መስጠት—"ለሚያምኑቱ ምሳሌ" (1 Timothy 4:12) መሆን እንደሆነ ገባኝ። እርሱ የሚጠይቀን ይህ ብቻ ነው፣ እናም ልሰጥ የምችለውም ይህ ብቻ ነው።

© 2011 በ Intellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/10 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/10 (እ.አ.አ)። *First Presidency Message, March 2011* (እ.አ.አ)። Amharic። 09767 506

# ወደ ቤተመቅደስ ኑ እናም በረከቶቻችሁን ተቀበሉ

እምነት • ቤተሰብ • እርዳታ

*ይህን መዝገብ አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው።*

እህቶች፣ ከሁሉም በላይ ተባርከናል። አዳኝ በእዚህች ቤተክርስቲያን መሪነት ቆሟል። በህያው ነብያት ተመርተናል። ቅዱሳት መጻህፍት አሉን። እናም ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ እንዲረዱን አስፈላጊ የሆኑ ስነስርዓቶችን ለማግኘት የምንችልባቸው ብዙ ቅዱስ ቤተመቅደሶች በአለም ውስጥ ሁሉ አሉን።

መጀመሪያ ወደ ቤተመቅደሱ ለእራሳችን እንሄዳለን። የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል የሆኑት ሽማግሌ ሮበርት ዲ ሔልስ እንደገለጹት፣ “የቤተመቅደስ ዋና አላማ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ ከፍ ከፍ ለመደረግ አስፈላጊ የሆኑትን ስነስርዓቶች ለመስጠት ነው። የቤተመቅደስ ስነስርዓቶች ወደ አዳኝ ይመሩናል እናም በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ በኩል የሚመጡትን በረከቶች ይሰጡናል። ቤተመቅደሶች ሰዎች ከሚያውቋቸው የመማሪያ ዩንቨርስቲ ሁሉ ታላቅ የሆኑ፣ ስለአለም ፍጥረት እውቀትና ጥበብ የሚሰጡን ናቸው። የመንፈሳዊ ስጦታ መመሪያዎች በእዚህ ስጋዊ ህይወታችንን እንዴት መኖር እንደሚገባን መመሪያ ይሰጡናል። . . . ስነስርዓቱ እንዴት መኖር እንደሚገባን የሚሰጠን መመሪያዎች እና አዳኞችንን በመከተል በጽድቅ ለመኖር የምንገባውን ቃል ኪዳን ያለው ነው።”[1]

ነገር ግን የቤተመቅደስ አገልግሎት በእዚህ አያልቅም። የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ፕሬዘደንት፣ ፕሬዘደንት ቦይድ ኬ ፓከር እንዳስተማሩት፣ “ከመጋረጃው አልፈው ለሄዱት በምትኩ በመሆን በመስራት፣ ቃል ኪዳን የገባችሁትን እንደገና ትገመግማላችሁ። ከጌታ ቤት ጋር የምታገናኙትን ታላቅ የመንፈስ በረከቶችን በአዕምሮአችሁ ውስጥ ታጠናክራላችሁ። . . . በቃል ኪዳኖች እና በስነስርዓቶች መሀከል ውስጥም በቅዱስ ቤተመቅደስ ውስጥ የምታገኙት በረከቶች አሉ።”[2]

ወደ ቤተመቅደስ ኑ እና እንደገናም ተመለሱ። የቤተመቅደስ ቃል ኪዳኖች የዘለአለም ህይወት በሆኑት ከሁሉም በላይ ታላቅ ወደ ሆኑት በረከቶች በሚመራን መንገድ ላይ ያቆየናል።

*የሴቶች መረዳጃ ማህበር አጠቃላይ ፕሬዘደንት ሁለተኛ አማካሪ ባርብራ ቶምሰን።*

## ከቅዱስ መጻህፍት

ኢሳይያስ 2፥3፤ 1 ቆሮንቶስ 11፥11፤ ራዕይ 7፥13–15፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 109

## ከታሪካችን

ነቢዩ ጆሴፍ በብዙ ጊዜ የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶችን ያነጋግር ነበር። የናቩ ቤተመቅደስ እየተገነባ እያለ፣ ነቢዩ እህቶችን በቤተመቅደስ ስነስርዓቶች በኩል ተጨማሪ እውቀቶችን ለመቀበል ለማዘጋጀት ትምህርቶችን አስተማራቸው። በ1842 (እ.እ.አ) ለመርሲ ፊልዲንግ ቶምሰን የመንፈስ ስጦታ “ለጭለማ ወደ አስደናቂ ብርሀን ያመጣሻል” አላት።[3]

ከ6 ሺህ በላይ የሚገመቱ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ከናቩ ተሰድደው ከመውጣታቸው በፊት የቤተመቅደስ ስነስርዓቶችን ተቀበሉ። ፕሬዘደንት ብሪገም ያንግ (1801–77) እንዳሉት፣ “[የቤተመቅደስ] ስነስርዓቶችን ለመቀበል ቅዱሳን ያሳዩት ጭንቀት፣ እና እነዚህን ላከናወኑላቸው የነበረን ጭንቀት ታላቅ ሆኖም፣ በየቀኑ በአማካይ አራት ሰዓት ብቻ በመተኛት እና በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ወደ ቤት በመሄድ፣ በቤተመቅደስ ውስጥ በቀን እና በምሽት ውስጥ የጌታን ስራ ወደ ማከናወን እራሴን አሳልፌ ሰጠሁ።”[4] የቤተመቅደስ ቃል ኪዳን ጥንካሬና ሀይል ከተማቸውን እና ቤተመቅደሳቸውን ወደማይታወቀው ለመጓዝ ሲሄዱ ቅዱሳንን ያጠናከሯል።

ማስታወሻዎች

1. ሮበርት ዲ ሔልስ፣ “Blessings of the Temple,” *Liahona,* ህዳር 2009፣ 14።
2. ቦይድ ኬ ፓከር፣ The Holy Temple (1980)፣ 170፣ 171።
3. የቤተክርስትያኗ ፕሬዘደንቶች ትምህርቶች፤ ጆሴፍ ስሚዝ [2007 (እ.እ.አ)]፣ 451።
4. Teachings of Presidents of the Church: Joseph Smith (2007)፣ 414።

### ምን ማድረግ እችላለሁ?

1. የምጎበኛቸውን “ወደ ቤተመቅደስ ለመምጣት” ባላቸው ውሳኔ እንዳጠናክራቸው ምን አጋጣሚ ከእነርሱ ጋር ልካፈል?

2. የቤተመቅደስ በረከቶችን ለእራሴ ለማግኘት እንዴት እችላለሁ?

ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org ሂዱ።

© 2011 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩኤስኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.እ.አ)። ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/10 (እ.እ.አ)። *Visiting Teaching Message, July 2011* Amharic። 09767 506